# የተሸጠው ሐዋርያ

**በመስከረም አንድ ቀን በቤተ ክርስቲያን ከዘመን መለወጫ ዐውደ ዓመትነቱ በተጨማሪ የቅዱስ ራጉኤል፣ የኢዮብ ጻድቅ እና የሐዋርያው ቅዱስ በርተሎሜዎስ በዓለ እረፍት የሚዘከርበት ቀን ነው:: ከነዚህ ውስጥ ለዛሬ የሐዋርያው በርተሎሜዎስን ታሪክ በመጠኑ እንመለከታለን::**

ቅዱስ በርተሎሜዎስ ትውልዱ ከነገደ ንፍታሌም ነው:: በገድለ ሐዋርያት ተጽፎ እንደምናገኘው ቅዱስ በርተሎሜዎስ በሐዋርያት ዕጣ የደረሰው አልዋህ በተባለ ሀገር ነበር:: ቅዱስ ጴጥሮስ በርተሎሜዎስን ለማድረስ ሲል አብረው ወደ አልዋህ ተጓዙ:: ሁለቱም ሀገሩን አያውቁትም ነበርና ጉዟቸው በጥየቃ ነበር::

በመጨረሻም አንድ ሲራራ ነጋዴ አገኙና እንዲያደርሳቸው ጠየቁት ነጋዴው ማንነታቸውን ሲጠይቃቸው የጌታችን ደቀመዛሙርት ክርስቲያኖች መሆናቸውን ነገሩት:: ያም ነጋዴ በመንገዱ የሰማውን አስታውሶ «እናንት ሐዋርያት ሰው ብቻውን ካልኖረ አይጸድቅም ትላላችሁ ደግሞም ባልና ሚስት ትለያያላችሁ ይባላል:: እውነት ነውን?» አለና ጠየቃቸው:: «እኔ በምንም መንገድ ወደ ሀገሬ አልወስዳችሁም፣ ደግሞ ሚስቴ ትምህርታችሁን የሰማች እንደሆነ ትታኝ ትኮብልል?» በማለት ትቷቸው ሄደ::

በዚህ ጊዜ ቅዱስ ጴጥሮስ እና ሐዋርያው በርተሎሜዎስ ተመካከሩ:: ሌላ ነጋዴ ሲመጣም ቅዱስ ጴጥሮስ «ይህን ባርያዬን በሀገረ አልዋህ ልሸጠው ፈልጌአለሁ እባክህ ወደ ሀገርህ ውሰደኝ ሲል ጠየቀው ያም ነጋዴ ለብዙ ጊዜ ከሀገሬ ወጥቼ የምኖር በመሆኔ ለቤቴ አገልጋይ የሚሆን ሰው አጥቼ እኖር ነበር:: ዛሬ አገኘሁ:: ለመሆኑ ሙያው ምንድን ነው?» ብሎ ጠየቃቸው ቅዱስ ጴጥሮስ ቀለል አድርጎ «ወይን ጠባቂ ነው» አለው:: ያ ነጋዴ እጅግ ብዙ ወይን ስለነበረው በ30 እስታቴር በርተሎሜዎስን ከቅዱስ ጴጥሮስ ገዛው ቅዱስ ጴጥሮስ ገንዘቡን ከነጋዴው ከተቀበለ በኋላ «አደራ ለሌላ ጌታ እንዳትሸጠው መከራም እንዳታበዛበት» ሲል ነጋዴውን ለመነው::

ባለጸጋው ግመሎቹን ሲያስተካክል ቅዱስ ጴጥሮስ ገንዘቡን ደብቆ ለበርተሎሜዎስ በመስጠት ለድኾች መጽውተው አለውና ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ:: ነጋዴውና በርተሎሜዎስ በበርሃ ውስጥ መንገዳቸውን ቀጠሉ:: አልዋሕ እንደደረሱም ነጋዴው በርተሎሜዎስን የወይን ጠባቂዎች አለቃ አድርጎ ሾመው ወይን እየጠበቀ፣ እየኮተኮተ እና እየተከለ ለ40 ቀናት ያህል በሥራ ተጠምዶ ተቀመጠ:: በዚህ ጊዜም «ጌታዬ ሆይ ወንጌልህን ሳልሰብክ፣ ትዕዛዝህን ሳልፈፅም ተቀምጬ መቅረቴ ነውን?» እያለ ያለቅስ ነበር::

አንድ ቀን ባለጸጋው የወይኑን ቦታ ሊያይ ሲመጣ እባብ ከጉድጓድ ወጥቶ ነከሰውና መርዙ ኃይለኛ ስለነበር በሰውነቱ ውስጥ ተሰራጭቶ ለሞት አበቃው:: ወዳጅ ዘመዶቹም ሊያለቅሱ ተሰበሰቡ:: በርተሎሜዎስ ግን ወደ እግዚአብሐር ይጸልይ ነበር:: የቤቱም ሰዎች «አንተ ጨካኝ አሽከር ጌታህ ሲሞት እንደማልቀስ አፍጥጠህ ታየናለህን?» እያለ ጮኹበት::

በርተሎሜዎስ ግን ጸሎቱን እስኪፈጽም ታገሣቸውና ያንን ባለጸጋ በስመ እግዚአብሔር ከሞት አስነሣው:: ያም ባለጸጋ ከእንቅልፉ እንደሚነቃ አፈፍ ብሎ ተነስቶ ለዚህ ያበቃው በርተሎሜዎስ መሆኑን መሰከረ:: በዚህም የተነሳ ባለጸጋውና የተሰበሰበውም ሕዝብ በተደረገው ተአምር ተገረሙ:: በበርተሎሜዎስ ስብከትም አምነው ተጠመቁ:: ከዚህ በኋላ በርተሎሜዎስ ረተስሚፌንና ሬኤንዶስ ወደተባሉ ሀገሮች አመራ:: እነዚህን ሀገሮች የሚገዛው የንጉሥ አክርጳ ሚስት እንኳን እስክትለወጥ ድረስ ብዙ ክርስቲያኖችን አፍርቷል:: መኳንንቱና መሳፍንቱ የሕዝቡን መለወጥ የአምልኮ ጣኦታቸውን መቅረት ሕዝቡም ከእነርሱ ይልቅ ለበርተሎሜዎስ ቃል መታዘዙን ተመልክተው በቅንዓት ተነሱበት::

ተከስሶም ወደ ንጉሥ አግሪጳ ፍርድ ቤት ቀረበ በዚያም የሞት ፍርድ ተፈረደበት:: መስከረም 1 ቀን አሸዋ በተሞላ ከረጢት ውስጥ ከትተው ከነሕይወቱ ባሕር ውስጥ ወረወሩት:: በዚያም ዐረፈ:: በነጋታውም ምእመናን ከባሕር አውጥተው ቀበሩት:: የቅዱሳን አባቶቻችን በረከት በሁላችን ላይ ይደር አሜን::

**ምንጭ «ቤተ ክርስቲያንህን ዕወቅ» መጽሐፍ ሰናፍጭ 7ኛ ዓመጽ ቁጥር 1**

**ማኅበረ ቅዱሳን**